# ቅናት እንዳይጠናወትህ ተጠንቀቅ!

***መመሪያ፦*** ይህን መልመጃ ጸጥታ በሰፈነበት ቦታ ሆነህ ሥራ። ጥቅሶቹን ስታነብ በቦታው እንዳለህ አድርገህ አስብ። ሁኔታውን በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል እንዲሁም በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ሰዎች ሲነጋገሩ ድምፃቸውን ለመስማትና ስሜታቸውን ለመረዳት ሞክር። ታሪኩ ሕያው እንዲሆንልህ አድርግ።

***ዋነኞቹ ባለታሪኮች፦*** ማርያም፣ አሮን፣ ሙሴ

***ታሪኩ በአጭሩ፦*** ማርያምና አሮን በቅናት ተነሳስተው በወንድማቸው በሙሴ ላይ አጉረመረሙ።

## 1 ሁኔታውን ለማስተዋል ሞክር።—ዘኍልቍ 12:1-15ን አንብብ።

በዚህ ዘገባ ላይ የተገለጹት ሦስት ባለታሪኮች ምን ዓይነት መልክና ባሕርይ ያላቸው ይመስልሃል?

ማርያም፦ ______________________________

አሮን፦ ______________________________

ሙሴ፦ ______________________________

ማርያምና አሮን በቁጥር 2 ላይ ያለውን ሐሳብ ሲናገሩ ምን ዓይነት የድምፅ ቃና የሚኖራቸው ይመስልሃል?

______________________________

‘የደመናው ዓምድ’ ምን ይመስል እንደነበረ በዓይነ ሕሊናህ ለማየት እንዲሁም ይሖዋ ማርያምንና አሮንን ሲቆጣቸው ድምፁ ምን ዓይነት እንደሚሆን ለማሰብ ሞክር። ከዚያም በዓይነ ሕሊናህ “ምን እንደታየህ” እንዲሁም “ምን እንደሰማህ” ግለጽ። (*ዘኍልቍ 12:5-9ን እንደገና አንብብ።*)

______________________________

አሮን እና ሙሴ ከቁጥር 11-13 ላይ ያለውን ሐሳብ በመግለጽ ማርያም እንድትፈወስ ይሖዋን ሲለምኑ ምን ዓይነት ስሜት የሚኖራቸው ይመስልሃል?

______________________________

## 2 ጥልቅ ምርምር አድርግ።

ከማርያም፣ ከአሮን እና ከሙሴ ታናሹ ማን ነው? ይህ ጉዳይ ማርያም እና አሮን ስለ ወንድማቸው እንደዚያ እንዲናገሩ ተጽዕኖ አሳድሮ ሊሆን እንደሚችል ይሰማሃል? (ዘፀአት 2:1-4, 10፤ 7:7)

______________________________

ማርያም እና አሮን “[ይሖዋ] በእኛስ አልተናገረም?” ብለው እንዲናገሩ ያደረጋቸው ምን ሊሆን ይችላል? (ፍንጭ፦ ዘፀአት 15:20, 21ን እና 28:1-3ን አንብብ።)

______________________________

ይሖዋ ማርያምንና አሮንን የተቆጣቸው ለምንድን ነው? (ዘኍልቍ 12:7, 8)

______________________________



www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

ሙሴ ለተሰነዘረበት ነቀፋ ምላሽ ከሰጠበት መንገድ የሚነካህ ነገር ምንድን ነው?

## 3 ከዚህ ታሪክ ያገኘሽውን ትምህርት ተግባራዊ አድርግ።

ከዚህ በታች ስለሰፈሩት ሐሳቦች ምን ትምህርት እንዳገኘህ ጻፍ፦

ቅናት ስላለው አደጋ

ነቀፋ ሲሰነዘርብን ምላሽ መስጠት ስለምንችልበት መንገድ

## 4 ራስህን ጠይቅ።

ቅናት ሊያድርብኝ የሚችለው በየትኞቹ መንገዶች ሊሆን ይችላል?

ነቀፋ ሲሰነዘርብኝ ጉዳዩን በገርነትና ፍቅር በሚንጸባረቅበት መንገድ መያዝ የምችለው እንዴት ነው?

ከዚህ ታሪክ የማገኘው ለእኔ በጣም አስፈላጊ የሆነው ትምህርት የትኛው ነው? ለምን?

**ተጨማሪ ሐሳብ፦** ከጓደኞችህ ወይም ከቤተሰብህ ጋር ሆነህ ይህን ታሪክ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡት። ተረካውን የሚያነብብ አንድ ሰው መምረጥ ትችላላችሁ። ሌሎቻችሁ ደግሞ ማርያምን፣ አሮንን፣ ሙሴን እና ይሖዋን ሆናችሁ ልታነብቡ ትችላላችሁ።



JW.ORG™

ይህን ፒዲኤፍ ከwww.jw.org/am ላይ አውርደህ ማተም ትችላለህ



www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania